# JICH-R-ፖሊሲ የተማሪዎች አደንዛዥ ዕጽ እና አልኮል መጠቀም

ሲጠቀሙ መገኘት

በትምህርት ቤቱ ቅጽር ግቢ ውስጥ ወይም በት/ቤቱ ተለይተው በተዘጋጁ ቦታዎች ወይም በስኩል ዲስትሪክቱ መጓጓዣ መኪናዎች በሚጓጓዙበት ጊዜ በአልኮል፣ ናርኮቲክስ ወይም ሌሎች ሕገወጥ አደገኛ ኬሚካል ንጥረ ነገሮች አእምሮዋቸው ናውዞ ወይም ሰክረው የሚገኙ ተማሪዎች ላይ የሚከተለው እርምጃ ይወሰዳል፥

1. አንድ የሆነ፣ ሕገወጥ አደገኛ ንጥረነገር በመጠቀሙ ምክንያት ሊሆን በሚችል ሁኔታ አንድ ተማሪ ያልተለመደ ባሕሪ ሲያሳይ፣ የት/ቤቱ ሠራተኛ ተማሪውን የሁኔታውን ከባድነት ደረጃ ወደ የሚወስነው የት/ቤቱ ነርስ ዘንድ ይዞት ይሄዳል።

a. ሁኔታው የተፈጠረው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከሆነ እና ተማሪው ደሕንነቱ እንደተጠበቀ ወደ ነርስ ቢሮ መሄድ የማይችል ሆኖ ሲገኝ፣ በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ወይም በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ለዚህ ጉዳይ የተመደቡ ሰዎች አስፈላጊው ድጋፍ እንዲሰጠው ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

b. ሁኔታው የተፈጠረው በማናቸውም በት/ቤቱ አስተዳደር ስር ባለ ከመማሪያ ክፍል ውጭ ያለ ቦታ ከሆነ፣ የት/ቤቱ ሠራተኛ ተማሪውን ወደ ት/ቤቱ ነርስ ሊወስደው ይገባል።

c. የት/ቤቱ ነርስ በቦታው ሳይገኝ ቢቀር፣ የተለመደው የድንገተኛ አደጋ እርዳታ አሰጣጥ አሰራር ለዚህ ጉዳይ በተመደቡት ሠራተኞች መፈጸም አለበት።

d. በአንድ ተማሪ ላይ ያልተለመደ ባሕሪ መኖሩን የተገነዘቡ የት/ቤቱ ሠራተኞች ሁኔታውን በአጭሩ ቀኑን፣ ጊዜውን እና ሁኔታው የተፈጠረበትን ቦታ በመጥቀስ በጽሑፍ ማስፈር አለባቸው። እንደዚህ ዓይነት ሰነዶች ከርዕሰ መምህሩ ጋር በጋራ ይዘጋጃሉ።

2. ርዕሰ መምህሩ ወይም ወኪሉ የተማሪውን ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች (ወይም በድንገተኛ አደጋ ጊዜ ተጠሪ ተብሎ በመታወቂያው ላይ የተጠቀሰውን ግለሰብ) በማግኘት ተማሪው ያልተለመደ ወይም አደገኛ ባሕሪ በማሳየት ላይ መሆኑን ያሳውቃል። ርዕሰ መምህሩ ወይም ወኪሉ የሚታየው ባሕሪ ምን እንደሚመስል ያብራራል እንጂ ለወላጆቹ መንስኤው ምን እንደሆነ ከድምዳሜ ላይ በመድረስ አይነግራቸውም።

3. ሁኔታው የሕክምና እርዳታ የሚያስፈልገው ከሆነ እና ወላጆችን ለማግኘት የተደረገው ጥረት ካልተሳካ፣ ርዕሰ መምህሩ ወይም ወኪሉ እገዛ ለማግኘት ወደ 911 ይደውላል። ወላጆችን ወይም ሌላ ተጨማሪ ድጋፍ በመጠበቅ ወቅት፣ ተማሪው በጭራሽ ለብቻው ሊተው አይገባም ሆኖም ግን የቅርብ ክትትል ሊደረግለት በሚችል ጸጥ ያለ ቦታ ላይ እንዲሆን መደረግ አለበት።

4. ተማሪው የሕክምና እርዳታ አስፈለገውም አላስፈለገውም፣ ርዕሰ መምህሩ ወይም ወኪሉ ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን ከማሳወቅ ባሻገር፣ መፈጸም ያለባቸውን አሰራሮች ተከትሎ ይፈጽማል። የሚከተሉትን ያደርጋል፥

a. የተማሪው ሁኔታ የሚፈቅድለት ከሆነ፣ ተገቢነት ያለው የሕክምና መፍትሔ ማግኘት እንዲቻል ችግሩን ከተማሪው ጋር መወያየት።

b. ለዴንቨር ፖሊስ መምሪያ እና ለ DPS ደሕንነት እና ጥበቃ መምሪያ ነገሩን ማሳወቅ።

በመጠቀሙ ምክንያት የሚወሰድ የዲስፕሊን እርምጃ

ከምርመራ በኋላ፣ ርዕሰ መምህሩ ተማሪው በአልኮል፣ ናርኮቲክስ ወይም ሌሎች ሕገወጥ አደገኛ ኬሚካል ንጥረ ነገሮች አእምሮው የናወዘ እና/ወይም የሰከረ እንደሆነ/እንደነበረ ካረጋገጠ፣ ለተፈጠረው ችግር ተገቢውን ቅጣት ለመስጠት፣ JK ፖሊሲ እና JK-R (የተማሪ ዲስፕሊን) ተፈጻሚ ይሆናሉ። የሚከተሉት እርምጃዎች ይወሰዳሉ፥

ርዕሰ መምህሩ ወይም ወኪሉ ከወላጅ ወይም ከአሳዳጊ እና ከተማሪው ጋር ይነጋገራል። ርዕሰ መምህሩ ወይም ወኪሉ የሚከተሉትን ያደርጋል፥

a. ያሉትን የዲስፕሊን ቅጣት እርምጃዎች ይገመግማል፣

b. እንደ ተገቢነቱ ተማሪው ወደ ሚመለከተው የት/ቤቱ ሠራተኛ ይልከዋል (ለምሳሌ፥ ማህበራዊ ሠራተኛ፣ የስነልቦና አማካሪ ወይም የተማሪ አማካሪ) ወይም ወደ ማህብረሰብ ድጋፍ ኤጀንሲ (ለምሳሌ፥ የቤተሰብ ምክር አገልግሎት፣ የአደንዛዥ ዕጽ ማስቆሚያ የሕክምና ፕሮግራም፣ ከአልኮል መመረዝ ነጻ ማድረጊያ ማዕከል)። ተማሪው የሚላከው ሌሎች ተማሪው ያለበት ሁኔታ የሚያስከትላቸው እርምጃዎች ተሟልተው ከተፈጸሙ በኋላ ሊሆን ይችላል።

c. ተመሳሳይ ጥፋቶች ዳግመኛ እንዳይፈጠሩ በወላጅ፣ በተማሪው እና በት/ቤቱ መወሰድ ስላለባቸው ጥንቃቄዎች እና ኃላፊነቶች በዝርዝር በመግለጽ የሚፈረምበት ሰነድ ማዘጋጀት። በተጨማሪ፣ ሰነዱ ተማሪው ታግዶ በሚቆይበት ጊዜ ማድረግ ስላሉበት ገንቢ እንቅስቃሴዎች እና ለዚህም የሚረዳውን ኤጀንሲ መጥቀስ አለበት፣

ይዞ መገኘት ወይም ማከፋፈል

በትምህርት ቤቱ ቅጽር ግቢ ውስጥ ወይም በት/ቤቱ ተለይተው በተዘጋጁ ቦታዎች ወይም በስኩል ዲስትሪክቱ መጓጓዣ መኪናዎች በሚጓጓዙበት ጊዜ በአልኮል፣ ናርኮቲክስ ወይም ሌሎች ሕገወጥ አደገኛ ኬሚካል ንጥረ ነገሮች ወይም እነዚህን መሰል ነገሮች የያዙ የግል ንብረቶችን ይዘው ወይም ሲሸጡ፣ ሲሰጡ ወይም ሲለዋወጡ የሚገኙ ተማሪዎች ላይ የሚከተለው እርምጃ ይወሰዳል፥

1. ማስረጃውን እና/ወይም ኮንትሮባንድ ዕቃው ላይ በመጀመሪያ የደረሰበት የት/ቤት ሠራተኛ ማስረጃውን እና/ወይም ኮንትሮባንድ ዕቃውን ስለመያዙ የሚከተሉትን ተጨባጭ እውነታዎች በሰነድ መመዝገብ አለበት። የሚዘጋጀው ሰነድ ማስረጃው እና/ወይም ኮንትሮባንድ ዕቃው በተማሪው እጅ ስለመገኘቱ በግልጽ ማስቀመጥ አለበት። ይህ ሲደረግ፣ የተማሪው ስም እና ሌሎች ማንነትን መገለጫ መረጃዎች፣ ማስረጃው እና/ወይም ኮንትሮባንድ ዕቃው የት ቦታ እንደተያዘ እንዲሁም ጉዳዩን በአጭሩ የሚገለጽ ማብራሪያ መጻፍ አለበት።

2. ማስረጃውን ወይም ኮንትሮባንድ ዕቃውን የያዘው የት/ቤቱ ሠራተኛ በአፋጣኝ ወደ ርዕሰ መምህሩ ወይም ወኪሉ መውሰድ እና ማስረከብ አለበት።

3. ርዕሰ መምህሩ ወይም ወኪሉ ማስረጃውን እና/ወይም ኮንትሮባንድ ዕቃውን አሽጎ ማስቀመጥ በሚያስችል ነገር ወይም በኤንቬሎፕ ውስጥ ማስቀመጥ አለበት። ኤንቬሎፑ ታሽጎ ዕቃውን በያዘው የት/ቤቱ ሠራተኛ እና በርዕሰ መምህሩ ወይም ወኪሉ ተፈርሞበት መቀመጥ አለበት። የተያዘው ኮንትሮባንድ ዕቃ ዝርዝር በሌላ የተለየ ኤንቬሎፕ ውስጥ ታሽጎ ለብቻው መቀመጥ አለበት።

4. ርዕሰ መምህሩ ጉዳዩን ለዴንቨር ፖሊስ መምሪያ ያሳውቃል ወይም ለዚህ ጉዳይ ኃላፊነቱን እንዲረከብ ስልጣን የተሰጠው ከሆነ ለ DPD የት/ቤት ግብዓቶች ሹም እና ለ DPS ደሕንነት እና ጥበቃ መምሪያ ያሳውቅ እና የተያዘውን ንብረት የሚመለከተው ሹም እንዲረከበው ይጠይቃል። ይህ ኤንቬሎፕ ለፖሊስ መኮንኑ በቀጥታ በርዕሰ መምህሩ ወይም በወኪሉ በእጅ መሰጠት ያለበት ሲሆን በኮንትሮባንድ የተያዘ አልኮል መጠጥ በት/ቤቱ መቀመጥ የለበትም።

5. ተጨማሪ ተገቢው ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ተማሪዎቹ የዴንቨር ፖሊስ መመሪያ መጥቶ እስኪረከባቸው በማገፊያ ቦታ ይቆያሉ።

6. ርዕሰ መምህሩ ወይም ወኪሉ ወላጆችን ወይም አሳዳጊን ያሳውቃል።

ለይዞ መገኘት ወይም ማከፋፈል ተግባር ዲስፕሊን እርምጃ

JK ፖሊሲ እና JK-R (የተማሪ ዲሲፕሊን) ሁኔታውን ለመቆጣጠር እና እርምጃ ለመውሰድ ሥራ ላይ ይውላሉ። በሚመለከተው የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲ ኤግዝቢት የተያዘው ማስረጃ እና/ወይም ኮንትሮባንድ ዕቃ በውስጡ

ናርኮቲክስ ወይም ሌላ አደገኛ ሕገወጥ ኬሚካል ንጥረነገር እንዳለው ሲያሳውቅ ወይም አልኮል ወይም አደንዛዥ ዕጽ የያዘ የግል ንብረት ሲያዝ፣ ርዕሰ መምህሩ ወይም ወኪሉ ምርመራውን ያጠናቅቃል።

ርዕሰ መምህሩ ተማሪው የዲስትሪክቱን ፖሊሲ በመጣስ አልኮል፣

ናርኮቲክስ ወይም ሌላ አደገኛ ሕገወጥ ኬሚካል ንጥረነገር ወይም አደንዛዥ ዕጽ የያዘ የግል ንብረት ይዞ ስለመገኘቱ እርግጠኛ ሲሆን፣ ከ JK ፖሊሲ እና JK-R ጋር ተስማሚ የሆነ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወስዳል። በተጨማሪ የሚከተሉት እርምጃዎች ይወሰዳሉ፥

a. እንደ ተገቢነቱ ተማሪውን ወደ ሚመለከተው የት/ቤቱ ሠራተኛ ይልከዋል (ለምሳሌ፥ ማህበራዊ ሠራተኛ፣ የስነልቦና አማካሪ ወይም የተማሪ አማካሪ) ወይም ወደ ማህበረሰብ ድጋፍ ኤጀንሲ (ለምሳሌ፥ የቤተሰብ ምክር አገልግሎት፣ የአደንዛዥ ዕጽ ማስቆሚያ የሕክምና ፕሮግራም፣ ከአልኮል መመረዝ ነጻ ማድረጊያ ፕሮግራም)። ተማሪው የሚላከው ሌሎች ተማሪው ያለበት ሁኔታ የሚያስከትላቸው እርምጃዎች ተሟልተው ከተፈጸሙ በኋላ ሊሆን ይችላል።

b. በተቻለ ፍጥነት ተገቢነት ያለው ሱፐር ኢንቴንደንት ስለ ጉዳይ እንዲያውቀው መደረግ አለበት።

c. ተመሳሳይ ጥፋቶች ዳግመኛ እንዳይፈጠሩ በወላጅ፣ በተማሪው እና በት/ቤቱ መወሰድ ስላለባቸው ጥንቃቄዎች እና ኃላፊነቶች በዝርዝር በመግለጽ የሚፈረምበት ሰነድ ማዘጋጀት። በተጨማሪ፣ ሰነዱ ታግዶ በሚቆይበት ጊዜ ማድረግ ስላሉበት ገንቢ እንቅስቃሴዎች እና ለዚህም የሚረዳውን ኤጀንሲ መጥቀስ አለበት።

ከት/ቤት በቦርድ ፖሊሲ መጣስ ምክንያት የመባረር እርምጃ ይወሰዳል፣ እና በግልጽ በተቀመጠ ሁኔታ ተገቢነት ሲኖራቸው JK ፖሊሲ እና JK-R ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

የጸደቀው ፌብሩዋሪ 1፣ 1983
የተሻሻለው በኦክቶበር 15፣ 2009

ተዛማጅ ዋቢዎች፥ JIH, Student Interrogations, Searches and Arrests

JKD/JKE, Suspension/Expulsion of Students

KFA, Public Conduct on School Property

CROSS REFS.: JIH, Student Interrogations, Searches and Arrests

JKD/JKE, Suspension/Expulsion of Students

KFA, Public Conduct on School Property